# ምስጋና ሊቸረው የሚገባ ሰናይ ተግባር

ብርሀን ይሁን ከልደታ 8/10/12

## ከግድቡ ፅንሰት -እስከ ህዝብ ድጋፍ

ለካ በእስከዛሬው ታሪካችን መንግሥትና ህዝብ በአንድ መንፈስ በጋራ መግባባት ሀገርን ለሚለውጥ ዓላማ መሰለፍ ተስኖን እንጂ ብንነጋገርና ብንተሳሰብ ሊከሰቱ አይችሉም የተባሉ ለውጦችን አምጥተንና የችግርን ጋራ ንደን ሀገራችንን ከብልፅግና ጐራ ለመቀላቀል ምን ያግደን ነበር? ስል ራሴን ጠየቅኩ ፡፡ይኽ ጥያቄ ወደ አዕምሮዬ የተወረወረው ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በስጦታ ያበረከትኩት የአንድ ወር ደመወዜ ወደ ቦንድ ተቀይሮና ከፍተኛ የመሥሪያ ቤቴ ኃላፊ በተገኙበት በምስጋና ሲሰጠኝ ነበር ይኸም ሁኔታ በትዝታ ወደ ኋላ መልሶ 2003 ዓ/ምን እንዳሰላስል ግድ አለኝ፡፡

አዎን ትዝ ይለኛል በኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር በ2003 መንግስት የአምስት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አዘጋጅቶ በየቦታው ህዝብን በማወያየት ላይ ነበር፡፡የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚለው ሀሳብ በራሱ አዲስ እንደመሆኑና በዚያው ሰሞን በቴሌቪዥን መስኮት ለአጭር ጊዜ በተወዳጅ የብሔር ብሔረሰቦች ሙዚቃ ታጅቦ ይቀርብ የነበረውን የቴሌቪዥን ስፖት ስመለከትና “ ከቀጣዮቹ አምስት ዓመታት በኋላ ሀገራችን ከስንዴ ልመናና ዕርዳታ ትላቀቃላች ፣ በምታመነጨው ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይልም ከራሷ አልፋ ለጐረቤትና ሌሎች ሀገሮች ትተርፋለች፣ ከተማ አቀፍና ሀገር አቋራጭ የባቡር መሠረተ ልማቶችን በመዘርጋት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስሩ ወደ ላቀ ደረጃ ይሸጋገራል ወዘተ....." የሚለውን መልዕክት ሳዳምጥ ስለ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽኑ ዕቅድ ምንነትና ይዘት ለማወቅ በወስጤ የተጫረውን ፍላጐት አናረው፡፡

የማይደርስ የለምና በ2003 ዓ/ም መጀመሪያ ወራት መሥሪያ ቤቴ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱና ከተቋማችን በሚጠበቁ ጉዳዮች ዙሪያ ከሠራተኞቼ ጋር ለመምከር መድረክ አዘጋጅቼያለሁና ተገኝታችሁ መወያየት፣መተቸትና ማዳበር ትችላላችሁ የሚል ማስታወቂያ አወጣ፡፡ይህንኑም ተከትሎ ለሁለት ቀናት የዘለቀ ሞቅ ያለ ገለፃ ፣ ውይይትና ክርክር አካሄድን፡፡ በውይይታችንም ይሄ ይሄ ጥሩ ነው ተጠናክሮ ይቀጥል፤ እነዚህ ደግሞ ጉድለት አላባቸውና ፈጥነው ይስተካከሉ ስንልም ለሰብሳቢዎቻችን ሀሳባችንን አቀረብን፡፡ ሰብሳቢዎቻችንም ላደረግነው ሞቅ ያለ ውይይትና ለሰጠነው ገንቢ አስተያየት ምስጋናቸውን በመቸር አስተያየቶቻችንን ለዕቅዱ ማዳበሪያ እንደግብዓት እንደሚጠቀሙበት ቃል ገቡልን፡፡

ይኸንን ውይይት ባደረግንበት ጊዜ ትዝ ከማሉኝ ጉዳዮች አንዱ ሁሉም ተሣታፊ በዕቅዱ ይዘትና ሊደረስ በታሰበባቸው ግቦች ዙሪያ ከፍተኛ መገረምና አድናቆት አድሮበታል፡፡ እንደ ስጋት ይነሳ የነበረው ጉዳይ ግን ይህንን ግዙፍ ዕቅድ በየትኛው አቅማችን እንተገብረዋለን? ይከብደናል የሚል ነበር፡፡ በወቅቱም ሰብሳቢዎቻችን የሰጡን ምላሽ መንግስትና ህዝብ በዕቅዱ አስፈላጊነትና ወሳኝነት ላይ የጋራ መግባባት ላይ ከደረሰንና ለተግባራዊነቱም በአብሮነት ከዘመትን ከዚህም የበለጡ አንፀባራቂ ድሎችን እናስመዘግባለንና የይቻላልን መንፈስ ሰንቃችሁ ለተግባራዊነቱ ከአሁኑ ወገባችሁን ጠበቅ አድርጉ የሚል ነበር ፡፡

የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በመሰረተ ልማት ወዘተ እጅግ የገዘፉና ለሀገሪቱ ህዳሴ መሰረት የሚሆኑ ውጥኖችን ያካተተ ሲሆን ከእነዚህም አንዱ የኃይል አቅርቦትን አሁን ከነበረበት 2100 ሜጋዋት አካባቢ በዕቅድ ዘመኑ 8000 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅምን በመፍጠር 10,000 ሜጋ ዋት ማድረስን ታሳቢ ያደረገ ነበር፡፡

ከዚህ ዕቅድ ጋር ተያይዞም በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ትልሙ ውስጥ የተፀነሰው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዕውን መሆን በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ይፋ ሆነ፡፡ እኔን ጨምሮ በዓባይ ጉዳይ ለዘመናት በቁጭትና በትካዜ አንጀቱ ሲያር የኖረው የሀገራችን ህዝብም የዚህን ታላቅ የልማት ክስተት ዜና ሲሰማ መሪና አደራጅ ሳያስፈልገው ከገጠር እስከ ከተማ አዋቂ ህፃን አርሶ አደር ከተሜ፣ ሠራተኛ ተማሪ ሳይልና ዕድሜ፣ ጾታ፣ ብሔር፣ ሃይማኖት ወዘተ..ሳይለያዩት ድጋፉን በሀገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እንዲገልፅ አስገደደው፡፡ በተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በአንድ ድምፅ ይህን ታላቅ የልማት እንደግፋለን ለፍፃሜውም እንተጋለን ሲሉ የድጋፍ ድምፃቸውን ከተለያዩ ማዕዘናት አስተጋቡ፡፡

## የሠራተኛው ልዩ ድጋፍና አስተዋጽኦ

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ዕውን መሆን ደስታ ተሰምቶት ድጋፉን ያልገለጸና ባለው አቅም፣ በገንዘብ፣ በዕውቀትና በጉልበት ለመደገፍ ቃል ያልገባ ዜጋ አለ ተብሎ ባይታመንም እንደ እኔ እምነት በተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች ያሳዩት ድጋፍና ያበረከቱት አስተዋጽኦ ግን በታሪካችን ላቅ ያለ ቦታን የሚይዝ ይመስለኛል፡፡

እንደሚታወቀው ሀገሪቱ ካላት ውስን የኢኮኖሚ አቅም የተነሳና ፈጣን ልማቷን ለማረጋገጥ መንግስት በተለያየ መንገድ ከሚሰበስበው ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚመድበው ለመሰረተ ልማት ወጪዎችና ለካፒታል በጀት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ ሠራተኞች በአንፃራዊነት በንግድ ስራና በተለያዩ ኢንቨስትመንቶች ተሰማርተው ከሚገኙ የሀገሪቱ ዜጎች ያነሰ ገቢ እንዲያገኙና በዚሁ እንዲተዳደሩ ግድ ብሏቸው ከሞላ ጎደል ከእጅ ወደ አፍ የሚሉት ዓይነት ኑሮ እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገታችንና ዓለም አቀፍ ክስተቶች ተደማምረው የፈጠሩት የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ከማንኛውም ዜጋ ይበልጥ ጫናቸውን ያሳረፉት በዚሁ ሰራተኛ ላይ እንደሆነም ግልጽ ነው፡፡

ይሁን እንጂ እኛ ሠራተኞች እነዚህና መሰል ጊዜያዊ ችግሮች ሳይበግሩን ሀገሬ ስታድግ አብሬ አድጋለሁና እኔ ዛሬ በምከፍለው መስዋዕትነት ለልጆቼ የተሻለች ኢትዮጵያን አስረክባለሁ ከሚል ልማታዊ ህሳቤ በመነሳት ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በቀዳሚነት የድጋፍ ድምጻችንን ከማሰማታችንም በላይ ከምናገኘው ገቢ ጋር ሲነፃፀር ከማንኛውም አካል የተሻለ የገንዘብ አስተዋጽኦ ለማድረግ ቃል ስንገባ የማንንም ምሪት ሳንፈልግና እንደ ዘመኑ ደርጉ የግዴታ መዋጮ ትዕዛዝ ሳይጫንብን ነበር፡፡

ሠራተኛው የኢትዮጵያን ህዳሴ ዕውን ለማድረግ የተጣላበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት በየስራ መስኩ ከሚያደርገው ደፋ ቀና በተጨማሪም ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ከአንድ እስከ ሶስት ወር የሚደርስ ደመወዙን በስጦታ በመለገስ በዓለምም ሆነ በሀገራችን የሲቪል ሰርቪስ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ የታሪክ

ገድል አስመዝግቧል፡፡ ይህ ስራውም ዘመንን ተሻግሮ በወደፊቱ ትውልድ የሚተረክ አኩሪ የታሪክ ቅርስ እንደሆነም አይጠረጠርም፡፡ትዝ ይለኛል ለዚሁ ታላቅ ግድብ የገንዘብ አስተዋጽኦ ለማድረግ በመስሪያ ቤታችን በተሰባሰብንበት ጊዜ ከሰራተኞች ፊት ላይ ይነበብ የነበረው ወኔና ደስታ ከዚህ በፊት አጋጥሞኝም ሆነ ተመልክቼው የማላውቀው ነበር። በዘመነ ደርግ ከአንዴም አራት አምስቴ ለእናት ሀገር ጥሪ እየተባለ ለጭፍጨፋ ደሞዛችን ይወሰድ የነበረው እንደዚህ በራሳችን ፍቃድ ተሰብስበንና ተወያይተን ሳይሆን ለእንዲህ ያለ ጉዳይ የሰራተኛው የአንድ ወር ደመወዝ እንዲቆረጥ ተወስኗል ተብሎ በመገናኛ ብዙሃን ሲነገር ነበር በሀዘን ዜናውን የምንሰማው።

## ለሠራተኞች ድጋፍ የመንግስት ምላሽ

እኛ ሰራተኞች ይህንን መሰሉን ሀገርና ወገን የሚኮራ ተግባር ስንፈጽም መንግስትም ድርሻውን እየተወጣ እንደነበር ይሰማኛል።ይህንንም እንድል ያስቻለኝ ምክንያት መንግስት ይህንን ታላቅ ፕሮጀክት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ በመተለም እውን አድርጎ ግንባታውን ከጀመረ በኋላ የታየውን ታላቅ ህዝባዊ የልማት መነሳሳት ላቅ ወዳለ ልማታዊ ተግባር ለማሸጋገር በማሰብና ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር በግድቡ ጠቀሜታ ዙሪያ የጋራ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችሉ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን ለማከናወን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ህዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ም/ቤትን በማቋቋሙና በምክር ቤቱም ከተለያዩ የህብረተሰብና የፖለቲካ ፓርቲዎች የተወከሉ ግለሰቦችን በማካተተም ለሥራው ስኬት ምቹ ሁኔታን በመፍጠሩ ነው፡፡

በተለይም የሀገሪቱ ሰራተኞች ካለችን ትንሽ አቅም ቆጥበን ላበረከትነው ምሳሌያዊ ድጋፍ ምስጋና በመቸር ይህንኑ አጋጣሚ በመጠቀም ሠራተኛው ሀገሩን እየጠቀመ የቁጠባ ባህሉን እንዲያጠናክር በማሰብ በስጦታ የተበረከተውን የገንዘብ ስጦታ ወደ ቦንድ ግዥ እንዲቀየር በማድረግ ለዜጎች ህይወት መቀየር ያለውን ተቆርቋሪነት አሳይቶናል፡፡ ይህም ተግባሩ እኔን ጨምሮ መላው ሰራተኞች ያልጠበቅነውና ያላሰብነው ነበርና ዜናውን ስንሰማ ከፍተኛ ደስታ እንዲፈጠርብን አድርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የመንግስት ሠራተኛውም ሆነ ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ያዋጣው ገንዘብ በትክክለኛ መስመር ለተፈላጊው ዓላማ እንዲውል በማሰብ ግልጽና ወጥ የሆነ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መፍጠሩና የሠራተኞችን መረጃ በሚገባ የማደራጀት ሥራም ማከናወኑ ያዋጣነውን ገንዘብ በሚያስተማምን መልኩ ለተገቢው ዓላማ ለማዋል ያለውን ቁርጠኝነትም ያመላክታል ብዬ አስባለሁ፡፡ ቦንዶችን የማሳተም ሥራዎችን በመስራትም ሰራተኛው ለቆጠበው ገንዘብ የቦንድ ሰርተፍኬት የሚሰጥበትን ሁኔታ ሲያመቻች ቆይቶ ለሠራተኞች ማከፋፈልም መጀመሩና ለሰራተኞች አስተዋጽኦ ልዩ ቦታ በመስጠትም የቦንድ አሰጣጡ ስነ-ሥርዓት በየተቋማቱ በምስጋና በታጀበ ስነ - ስርዓት እንዲከናወን ማድረጉም መንግስት ለዜጎች መልካም ሥራ ዕውቅና እንደሚሰጥ የሚመሰክር ተጨባጭ ማስረጃም ሆኖ አግኝቼዋለሁ ፡፡ ባለፈው ሰሞን ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም እኔ በምሰራበት መስሪያ ቤት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ክብር አቶ አለማየሁ ተገኑ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት በኤግዚቢሽን ማዕከል የተካሄደው የምስጋናና ቦንድ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ከላይ ለገለጽኩት አባባሌ ሰናይ ማስረጃ ነው፡፡

በስነ-ስርዓቱ ላይ ከሠራተኞች ፊት ይነበብ የነበረው የደስታና የታሪክ ሰሪነት ስሜት ለትክክለኛና ሀገርን ለሚለውጥ ዓላማ መሰለፍ ምን ዓይነት እርካታን እንደሚያጎናጽፍ በግልጽ ያሳየ ነበር፡፡ ይህ ሁነት ሙሉ ጊዜያቸውን ለአሉባልታ ሰውተው መንግስት ከሰራተኛው ለሰበሰበው ገንዘብ ቦንድ አይሰጥም ወዘተ የሚል የሀሰት የፈጠራ ወሬ ሲያሰራጩና ሀገርን ለመለወጥ ከተያያዝነው መልካም ጎዳና ሊያዘናጉን የሞከሩ ኃይሎችን ማንነትም

በገሀዱ አሳይቶ አልፏል ብዬ አምናለሁ፡፡ እነዚህንና መሰል በርካታ ተግባራትን በማከናወኑም ነው ከላይ መንግስት የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እየተወጣ ነውና ምስጋና ሊቸረው ይገባል እንድል የገፋፋኝ።

## በቀጣይስ ከሰራተኛው ምን ይጠበቃል?

እዚህ ላይ ለውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትና ተጠሪዎቹ ሰራተኞች በተዘጋጀው የቦንድ አሰጣጥና የምስጋና ስነ-ሥርዓት ላይ የግድቡ ሥራ አሲኪያጅ ኢንጂነር ስመኘው በቀለ ያስተላለፉትን መልዕክት ማስታወሱ ከሰራተኛውም ሆነ ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ምን እንደሚጠበቅ በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላል ብዬ አምናለሁ፡፡ ኢንጂነር ስመኘው በዕለቱ እንደተናገሩት "የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ሀሳብ አፍላቂነትና ድጋፍ የአንድ ዓመት ከአራት ወር ስኬታማ ግዜያትን አሳልፏል፡፡ በሌላ አነጋገር ግድቡን የአንድ ዓመት ከአራት ወር ህጻን አድርገን እንወስደውና ለዚህ ጨቅላ እንዴት ያለ እንክብካቤና ክትትል ተደርጎለት ሙሉ ሰው ደረጃ ማድረስ እንደሚገባ አስቡት፡፡ የሚፈልገው የዕለት ከዕለት ክትትላችሁንና ድጋፋችሁን ነውና አሁን የጀመራችሁትን ይህን አኩሪ ተግባር አጠናክራችሁ ቀጥሉ፡፡እኛም ለፍሬ ለማብቃት ያለምንም ዕረፍት ሌት ተቀን እንረባረባለን" ሲሉ ነበር መልዕክታቸውን ያስተላለፉት፡፡ አባባላቸው እውነትነት አለው ምክንያቱም ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለፍሬ በቅቶ ውጤቱን ለመመልከት ድፍን አምስት ዓመታት ያስፈልጉታልና፡፡

በመሆኑም እኔን ጨምሮ መላው ሰራተኛ ከዚህ ቀደም ያሳየነውን አኩሪ የልማት ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት አጠናክረን በማስቀጠል ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እንደ ዓይናችን ብሌን የምንሳሳለትንና የህዳሴ ጉዟችንን የሚያፋጥንልንን ይህን ግድብ እውን ለማድረግ የጀመርነውን የቦንድ ግዥ እስከፍፃሜ አጠናክረን አድንቀጥል እንደ አስፈላጊነቱም የጉልበትና የዕውቀት ድጋፋችን ማበርከታችንን እንግፋበት እላለሁ፡፡ ገና ከጠዋቱ ህሳቤያችንም ሆነ ዓላማችን እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን የሚል ነበርና፡፡ከዚህ በተጨማሪም በሀገራችን የተጀማመሩ አንጊ የልማት ውጥኖች ከግብ ሊደርሱ የሚችሉት በየተሰማራንበት የሥራ ዘርፍ መልካም ሥነ ምግባርን በመላበስ ደንበኞቻችንን ማስተናገድ ስንችል ነውና በየተቋማችን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባናልም እላለሁ፡፡

## ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችስ ከእኛ ከሠራተኞች ምን ይማራሉ?

በፀሀፊው እምነት በግልም ሆነ በመንግስት ተቋማት ከሚሰሩ ሰራተኞች ሌሎች ዜጎች ትምህርት ሊቀስምባቸው የሚገቡ በርካታ ቁምነገሮች አሉ ብዬ አምናለሁ፡፡

ለምሳሌም ያህል እኛ ሰራተኞች ሀገራችንንና የሀገራችንን ልማት በመደገፍ በቀዳሚነት ያለምንም ግፊትና ትዕዛዝ ከ1/12ኛ-3/12ኛ የሚደርስ ደመወዛችንን የለገስነው በቂ ገቢ ኖሮን፣ የተደላደለ ኖሮ ኖረንና መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ሆኖልን አልነበረም፡፡ ይልቁንም ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት እኛ ሰራተኞች በአንፃራዊነት አነስተኛ ገቢ ያለን፣ የኑሮ ውድነት ከፍተኛውን ጫና ያሳደረብንና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የኑሮ ዘይቤ የምንኖር ነን፡ ፡ ይሁንና ነገ ከዛሬ የተሻለ መሆኑን በማመንና የሀገር ልማት ዕውን የሚሆነው ጊዜያዊ ችግሮቻችንን ተቋቁመንና መጪውንና ብሩሁን ጊዜ በመመልከት መሆኑን በመገንዘብ ከዕለት ጉርሳችን ቀንሰንና ትልቅ መስዋዕትነት ከፍለን የገባውነን ቃል ተግባራዊ አድርገናል፡፡ ዘላለማዊ ምስጋና የሚገባው አብነታዊ የተግባር ድጋፍ፡፡

ይህንንም ሁኔታ ስንመለከት በተለይም ባለፉት 21 ዓመታት በተመቻቸው የነፃ ኢኮኖሚ ሥርዓትና ሀብት የማፍራት መብት ተጠቅመው ሚሊኒየርና ቢሊየነር የሆኑ ባለ ሀብቶቻችን፣ በገጠርና ግብርና የልማት ፖሊስና ስትራቴጂ ታግዘው ባለ ሚሊዮን የሆኑ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮቻችን፣ በተለያየ የዓለም ክፍል ነዋሪ የሆኑና በተነፃፃሪ የተሻለ ገቢ ያላቸው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለሀገራችን ምን እያደረግን ነው ያለነው ብለው እንዲያስቡና ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ከእኛ ከሰራተኞች ተሳትፎ ጋር አነጻጽረው ሊመዝኑትና የበለጠ ለማድረግ ሊነሳሱ ይገባል የሚል እምነት አለኝ፡፡ በጋራ የምናፍርባትም ሆነ የምንኮራባት ሀገራችን የኩራቷም ሆነ የውርደቷ ምክንያቶች የምንሆን እኛው ዜጎቿ ነንና ጎበዝ በተቀደደልን የልማትና የዕድገት ጎዳና ተጉዘንና ሰራተኞች ለታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ያሳዩትን አርኣያነት ተከትለን የሀገራችንን ህዳሴ እናፋጥን ለልጆቻችንም የተሻለች ኢትዮጵያን እናስረክብ በሚል መልዕክት ጽሁፌን እቋጫለሁ፡፡